ቀን 03/7/2000 ዓም

ለሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ
የድጋፍ ሠጪ ድርጅቶች ማህበር

ጉዳዩ፡- የፓርቲያችንን የሠላማዊ የትግል ሥልት ይመለከታል፣

እኛ ኢትዮጵያውያን እጅግ የምንኩራበት የረጅም ዘመን የመንግሥትና የህዝብ አስተዳደር ታሪክ ያለን የመሆኑን ያክል ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር ተረጋግጦበታል የምንለውና በታሪክ ሂደት ውስጥ ነጥለን የምናወጣው ወቅት አላገኘንም። ከዚህም ጋር በተቆራኘ ሁኔታ መንግሥትን በድምጽ ስለማቀያየር ወይም የህዝብ ፍላጎትን በኮሮጆ ስለማስፈፀም እንደ ኢትዮጵያውያን ያለን እምነት እጅግ አነስተኛ ሆኖ ቆይቷል። እንግዲህ በዚህ የፖለቲካ ድባብ ውስጥ ነው ቅንጅት ዜጎች እንደነፃ ሰው ያላቸውን መብት ለመጠቀም ቁርጠኝነት አስከአሳዩና በአንድላይ እስከተነሱ ድረስ የትኛውንም አይነት ጉልበተኛ የማያብረከርኩበት፣ ፍላጎታቸውንም በሠላማዊ መንገድ እውን የማያደርጉበት አንዳች ምክንያት የለም ሲል ጠንካራ ሠላማዊ ታጋይ ሆኖ በአማራጭነት የመጣው።

ይህን የቅንጅት የሠላማዊ ትግል እንቅስቃሴ በመደገፍ በአለም ዙሪያ የሚገኙ ድጋፍ ሠጪ ድርጅቶቻችን ሲያደረጉ የቆዩት እገዛም በዚሁ የትግል ስልት ላይ ያላቸውን እምነት ያረጋገጠ መሆኑ ይታወቃል።

በስፋት የሚታየው ሁኔታ ይህ ቢሆንም የፓርቲው መሪዎች በእስር መቆየትን እና የኢህአዴግን በኢ-ዴሞክራሲያዊነት ፀንቶ መቀጠልን ብቻ ታሳቢ በማድረግ አንዳንድ በውጪ ሀገር የሚገኙ ደጋፊዎቻችን በትግል ስልቱ ላይ ጥያቄ ሲያነሱ በመስተዋላቸው የድርጅቱን አቋም ማብራራት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

በመሠረቱ በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ እሳቤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዋናው ተልዕኮ የመንግሥት ሥልጣንን በሕዝብ ፈቃድና በሕዝብ ምርጫ በሕግ ለተወሰነ ጊዜ ተረክቦ የተሻሉ በሚሉአቸው የፖሊሲ አማራጮች ሀገርን ማስተዳደር ነው። የፖለቲካ

ፓርቲዎች በእውነት በዚህ አስተሳሰብ የሚያምኑ ከሆነና በምርጫ የሚደረገውን የሕዝብን ዳኝነት የሚቀበሉ ከሆነ በጉልበት ሥልጣንን የመያዝ ፍላጎት ከየት ይመጣል? አብዛኛውን ጊዜ የትጥቅ ትግልን ለመጀመር የሚሰጠው ምክንያት በአገዛዝ መንበሩ ላይ ያለው ቡድን ለሕዝብ መብቶችና ፍላጎቶች ደንታ የሌለውና ለሕዝብ ፈቃድ የማይገዛ ስለሆነ ራሱ በሚያምንበት የኃይል እርምጃ መወገድ አለበት የሚል ነው:: ሠላማዊ ትግል ብዙና የተለያዩ እንቅፋቶች እንደሚያጋጥሙትና በሂደቱም ሕዝብን መስዋትነት የሚያስከፍል መሆኑ አያከራክርም:: የሚያከራክረው በሠላማዊ ትግል ሥልጣንን መያዝ ካልተቻለ በትጥቅ ትግል መሞከር ያስፈልጋል ወይም ይገባል የሚለው እምነት ነው:: በአብዛኛው ይህ አካሄድ ከንዴት፣ ከዓላማ መላላትና ከእልህ የሚመነጭ እምነት ነው:: ወደ ትክክለኛና ሕጋዊው ሥልጣን የሚያመራው አንድ መንገድ ብቻ ነው:: ይህም በአብዛኛው ሕዝብ ፈቃድና ምርጫ ላይ ብቻ ተመሥርቶ የሚገኝ ሥልጣን ነው:: በዚህ መንገድ ለውጡ የሰዎች ብቻ ሳይሆን የሥርዓትም ይሆናል:: በጉልበት መንገድ ሥልጣንን ለመያዝ በሚሞከርበት ጊዜ ሥልጣንን የሚነጠቀው በመንበሩ ላይ ያለው አምባገነን ብቻ አይደለም:: ሕዝቡም ነው:: የሚለወጠውም ሥርዓቱ ሳይሆን ሰው ነው:: የበላው በአልበላው ይተካል፣ አሮጌው ዘራፊና ግፈኛ በአዲስ ዘራፊና ግፈኛ ይቀየራል::

በሠለጠኑ ሀገሮች ሰዎችን መለዋወጥ ብቻ ዓላማ ሊሆን ይችላል:: እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሀገሮች ግን ከሰዎች ይበልጥ የሥርዓት ለውጥ አስፈላጊ ነው:: ሁላችንም ከአንድ ባህል የተቀዳን ነን:: ይህ ባህል ገዳይን እንደ ጀግና ከማወደስ ገና አልተላቀቀም:: ሠላማዊ የፖለቲካ ትግል የሚያስፈልገው ሁላችንንም (ገገርውንም ተቀናቃኙንም) ከዚህ በጣም ኋላ ቀር ባህል ነፃ ለማውጣት ነው::

ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ በምንም ዓይነት መንገድ በወንድማማቾች መሀከል ጦርነት እንዲካሄድ አይፈልግም:: እንዲያውም ወደ ትጥቅ ትግል የገቡት ሁሉ ከዚያ የወገን ሕይወትን ከሚያጠፋና ንብረትን ከሚያወድም ትግል ወደሠላማዊ ትግል የሚመለሱበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚገባ አጥብቆ ያምናል:: ለዚህም ይታገላል:: የሕዝብ ፈቃድ ሆኖ ሥልጣን ከያዘም በትጥቅ ትግል ላይ ላሉት ሁሉ ሙሉ ዋስትና ሰጥቶ ወደ ሠላማዊ ትግል እንዲገቡ ጥረት ያደረጋል::

የትጥቅ ትግል በኢትዮጵያ ፈጽሞ እንዳይጀመርና የተጀመረውም በፍጥነት በፖለቲካ መፍትሔ እንዲቋረጥ ከማድረግና ሠላማዊ የፖለቲካ ትግልን ከማበረታታት አንፃር ገዢው ቡድን ትልቅ ኃላፊነት አለበት:: በኃይል የመተማመኑንና ነፃነትን የማዳፈኑን ዘዴ ፈጽሞ በመተውና የማውቅልህ እኔ ብቻ ነኝ የሚለውን የማያዋጣ መንገድ በመለወጥ የመተማመን

በር መክፈት የግድ ያስፈልጋል። ከሁሉም በላይ ገዢው ፓርቲ በሕገ-መንግሥቱ የተደነገገውን መንግሥትን በሠላማዊ ምርጫ የመለወጡን መብት ሊቀበለው ይገባል።

ብዙ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ መሪዎች በጉልበት መንግሥትን ለመገልበጥ ሞክረዋል በሚልና በሌሎችም ሰበቦች ተከስሰው የዕድሜ ልክ እስራት እንደተፈረደባቸውና በምሕረትም እንደተለቀቁ በሰፊው ተነግሯል።

እውነቱ ትናንትም ሆነ ዛሬ ቅንጅት የተመሠረተው በሠላም ላይ መሆኑ ነው። ቅንጅት የተፈጠረው የኢትዮጵያን ሕዝብ የአገሩ ባለቤትና የአገሩ የሥልጣን ምንጭ ለማድረግ ነው ብሎም የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥልጣን ትግል ወደ ሥልጡን የፖለቲካ ትግል በመለወጥ በኢትዮጵያ ታሪክ የማይታወቀውን ሠላማዊና ሕዝባዊ የፖለቲካ ትግል ለማስለመድ ነው። ቅንጅት የተመሠረተው ታሪካችንንና ባህላችንን ያጎደፈውንና እድገታችንን የገታውን በጠመንጃ በመፋለምና በመጋደል የሥልጣን ባለቤት መሆንን ለማስቀረት ነው።

ስናጠቃልለው ቅንጅት የሠላማዊ ትግል ብቸኛ አማራጭ ነው የሚልበት ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉት፡-

- በኢትዮጵያ ታሪክ እስካለንበት ጊዜ ድረስ ወደሥልጣን መንበሩ የሚያመራው ወይ የመለኮታዊ ትዕዛዝ በማስመሰል፣ ወይ በጠመንጃ ኃይል ነው። ይህ መንገድ ያልሠለጠኑና ኋላ ቀር የሆኑ ሕዝቦች ሁሉ የሚጠቀሙበት፣ ከመጠላላት፣ ከመገዳደልና ከመደህየት በቀር ምንም ፋይዳ ያላስገኘ መካን ዘዴ ነው። ቅንጅት የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዚህ የጥፋት መንገድ ለማውጣትና በሥልጡን ሕዝብ መንገድ ወደ እድገትና ወደ ብልጽግና እንዲራመድ ለማድረግ የቆረጠና ፍጹም ሠላማዊ ለሆነ የፖለቲካ ትግል የቆመ የፖለቲካ ድርጅት ነው።

- ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞራሲ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት የቆመ የፖለቲካ ድርጅት ነው። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሳይፈራና ሳይሸማቀቅ በሙሉ ልብ በመብቶቹና በነፃነቱ እየተጠቀመ የአዕምሮውን ፍሬ ለሀገር ልማት እንዲያውል ያበረታታል። ነፃነትንና ልበ-ሙሉነትን የዜጎች ሀብት ለማድረግ ጠመንጃን መጠቀም በፍጹም የማይቻል ነው። ስለዚህም ነፃነትን በጉልበት የሚያፍኑ ኃይሎችን እየተቃወሙ በዚያው አይነት መንገድ (ማለትም በጉልበት) ነፃነትን እናመጣለን ማለት የአስተሳሰብ ቅራኔ ውስጥ የሚያስገባ ነው። ዜጎች ሁሉ በነፃነት ምርጫቸውን መግለጽ የሚችሉት በሠላማዊ ትግል ብቻ፣ የዜጎች ነፃነት የሚመጣውም በዚሁ መንገድ ብቻ ነው።

- የኢትዮጵያ ሕዝብ በጭቆና አገዛዝ ሥርና በጠመንጃ ኃይል መብቶቹንና ነፃነቱን ተገፍፎ የሚገኝ ስለሆነ በጠመንጃ ኃይል ለውጥ ለማምጣት እታገላለሁ የሚል ቡድን ሌላ ቢቀር በዘዴው ከጨቋኙ ቡድን ጋር አንድ ሆነ ማለት ነው:: ጭቆናን እታገላለሁ የሚል የጭቆናን ዘዴ ሲቀበል የመንፈስ እና የሞራል የበላይነቱን ያጣና ከጨቋኙ ጋር በአንድ የውድቀት ደረጃ ላይ ይቆማል:: በጉልበት የማስገደድ ዘዴ ለአንዱ መጥፎ ሌላው ደግሞ ጥሩ ሊሆን አይችልም:: የማንንም ሀሳብ ሆነ አቋም በጉልበት ወይም በጠመንጃ ማስለወጥ ማንም ቢያደርገው ተግባሩ ያው ነው::

በመሆኑም ቅንጅት የኢትዮጵያን የፖለቲካ ታሪክ ወደ ሥልጡን ፖለቲካ፣ ዜጎችን ወደ ነፃነትና ብልጽግና እራሱንም ወደ ላቀ ጥንካሬና ዴሞክራሲያዊነት ለማሳደግና ለማሸጋገር ብቸኛው መንገድ የሠላማዊ ትግል ብቻ መሆኑን እንደሚያምን ደግሞ እያረጋገጠ በዚሁ ዓላማ ዙሪያ በመሰባሰብ ለሚደረገው ትግል የድጋፍ ድርጅቶቻችን የሚያደርጉትን የፖለቲካ፣ የዲፕሎማሲ እና የፋይናንስ እገዛ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ፓርቲው ይጠይቃል::

ከአክብሮት ጋር

ብርቱካን ሚደቅሳ

የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

ተ/ም/ሊቀመንበር